የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

፴፪ኛ ዓመት ቁጥር ፲፬
አዲስ አበባ የካቲት ፭ ቀን ፪ሺ፲፰

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

32th Year No. 14
ADDIS ABABA, 12th February, 2026

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻፫/፪ሺ፲፰

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በቻይና ህዝባዊ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገውን የፍርደኞችን ማስተላለፍ ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ……………………………...................................................ገጽ ፲፱ሺ፭፻፳፩

## Content

Proclamation No. 1403/2026

Transfer of Sentenced Persons Treaty between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the People's Republic of China ratification Proclamation............................Page 19521

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻፫/፪ሺ፲፰

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በቻይና ሕዝባዊ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገውን የፍርደኞችን ማስተላለፍ ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በቻይና ሕዝባዊ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የፍርደኞችን ማስተላለፍ ስምምነት ነሐሴ ፴ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም በቤጅንግ- ቻይና የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥር ፲፬ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም ባካሄደው ፱ኛ መደበኛ ስብሰባ ያጸደቀው በመሆኑ፤

## PROCLAMATION No. 1403/2026

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE TRANSFER OF SENTENCED PERSONS TREATY BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE PEOPLE'S REPUBLIC OF CHINA**

**WHEREAS**, the Transfer of Sentenced Persons Treaty between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the People's Republic of China has been signed in Beijing- China, on the 5th day of September, 2024;

**WHEREAS**, the House of Peoples Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified this agreement at its 9th regular session held on 22nd day of January, 2026;

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55 Sub Articles (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby Proclaimed as follows.

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በህዝባዊ ሪፐብሊክ ቻይና መንግስት መካከል የተደረገውን ፍርደኞችን ማስተላለፍ ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻፫/፪ሺ፲፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "Transfer of Sentenced Persons Treaty between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the People's Republic of China ratification Proclamation No.1403/2026".

**፪. <u>ስምምነቱ ስለመጽደቁ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በቻይና ህዝባዊ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል ነሐሴ ፴ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም በቤጅንግ-ቻይና የተፈረመው የፍርደኞችን ማስተላለፍ ስምምነት ፀድቋል፡፡

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The Transfer of Sentenced Persons Treaty signed in Beijing on the 5th day of September, 2024 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the People's Republic of China is hereby ratified.

**፫. <u>የኢፌዲሪ ፍትህ ሚኒስቴር ኃላፊነት</u>**

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፍትሕ ሚኒስቴር ይህን ስምምነት ለማስፈጸም አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን ሁሉ እንዲወስድ በዚህ አዋጅ ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡

**3. <u>Responsibility of the FDRE Ministry of Justice</u>**

The FDRE Ministry of Justice is hereby empowered to undertake all acts necessary for the implementation of the Treaty.

**፬. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል::

**4. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall come into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**አዲስ አበባ የካቲት ፭ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም**

**ታዬ አጽቀሥላሴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**Done at Addis Ababa, On this 12th day of February, 2026**

**TAYE ATSKE SELASSIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**